የማዕድን ዘርፍ የሙስና ሥጋት ግምገማዊ ጥናት

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

1993

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ሚያዝያ /2015ዓም
አዲስ አበባ

ማውጫ

ቁጥር	ርእስ/ንኡስ ርእስ	ገፅ
ክፍል አንድ	መግቢያ	3
1.1.	የጥናቱ ዳራ (Backgraound Of The Study)	3
1.2.	የዘርፉ አጠቃላይ መረጃ	4
1.3.	የጥናቱ ዓላማ	6
1.4.	የጥናቱ ወሰን	6
1.5.	የጥናቱ አስፈላጊነት	6
ክፍል ሁለት	ተዘማጅ ፅሁፎች ትንተና	7
ክፍል ሶስት	የጥናቱ መረጃ አሰባሰብ ሂደትና ትንተና ዘዴ	8
3.1.	የጥናቱ ንድፈ-ሃሳብ (Research design)	8
3.2.	የጥናቱ ተሳታፊዎች እና የንሞና ዘዴ (Study Participants and Sampling)	8
3.3.	መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (Data collection methods)	8
3.4.	የመረጃዎችን ትንተና ዘዴ	10
ክፍል አራት	የሙስና ስጋት ትንተና	11
4.1.	የተቋማት አደረጃጀት	11
4.2.	ተጠያቂነትን ማስፈን	14
4.3.	የተቋማት ግልጽነት	15
4.4.	አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ	17
4.5.	የተቋማት ንብረት አስተዳደር	18
4.6.	የግዥ አስተዳደር	20
4.7.	የሰው ሃብት አስተዳደር	21
4.8.	የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ	23
4.9.	የፕሮጀክቶች አስተዳደር	23
4.10.	ኦዲትና ቁጥጥር	23
4.11.	የሙስና ስጋት	25
ክፍል አምስት	መደምደሚያ እና የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ	27
5.1.	መደምደሚያ	27
5.2.	የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ	28

ክፍል አንድ

መግቢያ

ይህ የሙስና ስጋት ጥናት ማዕድን ዘርፍ ስር የሚከገኙ የማዕድን ሚኒስቴር፣የኢትዮጵያ ጅኦሎጅካል ኢንስቲትዩትና የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ተቋማት ላይ የተካሄደ ሲሆን በዓምስት ምእራፎች የከፋፈለ ነው፡፡

1.1. የጥናቱ ዳራ (Backgraound Of The Study)

ሙስና በአደራ የተሰጠ ስልጣንና ኃላፊነትን ያለ አግባብ በመገልገል የህዝብና የመንግስት ሁለንተናዊ ስርዓትን የሚያዛባና ፍትህን የሚሸረሽር ድንበር ተሻጋሪ ወንጀል በመሆኑ ሀገራት ይህን ወንጀል መከላከል የሚያችል ዓለማቀፋዊ፣ አህጉራዊና ቀጠናዊ በቅንጅትና ትብብር በመፍጠር በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ መንግስት ይህን ወንጀል መከላከል የሚያስችል የትኩረት አቅጣጫ በመቀየስ በመስራት ላይ የሚገኝ ሲሆን የፌደራል የሥነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽንም ከመንግስት የተሰጠውን ተልዕኮ ማሳካት የሚያስችሉ ዘርፍ ተኮር የሙስና መከላከል ስልቶችን በመንደፍ እየሰራ ይገኛል፡፡

ከዘርፍ ተኮር የሙስና መከላከያ ስልቶች አንዱ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ጥናት ማካሄድ ነው፡፡ ተቋማት የአሰራር ስርዓት ቢዘረጉም፣ በየጊዜው ደንብና መመሪያ የሚያሻሽሉ ቢሆንም ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንጻር እዚህ ግባ የሚባል ለውጥ ማምጣት አልቻሉም፡፡ ለዚህ ሃሳብ ማጠናከሪያ የሚሆኑት ጉዳዮችን ስናይ፡ ማህበረሰቡ በመንግሰት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ቅሬታ እያሰማ መሆኑ፣ ዜጎች በመንግስት ተቋማት አመኔታቸው እየቀነሰ መምጣቱ፣ የአገልግሎት አሰጣጥ መጓተት፣ ተደጋጋሚ ኦዲት ግኝቶ መበራከትና የመሻሻያ ሀሳቦችን አለመተግበር፣ የገበያ ስርዓቱ ከሙስና ስጋት የተላቀቀ አለመሆኑ፣የተጠያቂነት ማነስ ጥቂት ማሳያዎች ናቸው፡፡

በመንግስት ተቋማት ለሚታዩት የሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ማነስ፣ የህግ የበላይነት መሸርሸር ፣ ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር አለመኖር ፣ የግልፅነትና ተጠያቂነት ስዓት ማነስ እንደመንስኤ የሚነሱ ናቸው፡፡ በዚህ ምክንያት የፌደራል የስነምግባርና የፀረሙስና ኮሚሽን በማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 3

ላይ የተቋማት የሙስና ስጋት ዳሰሳ ጥናት በማካሄድ ውጤቱን ለህዝብ ይፋ እንደሚያደርግ በተደነገገው መሰረት የኢፌድሪ ማዕድን ሚኒስቴር፣ የኢትየጵያ ጅኦሎጂካል ኢኒስቲቲዩት እና የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት አሰራርና አደረጃጀት፣ የተጠያቂነት ስርዓት፣ የተቋማት ግልፅነት፣ የአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ዝግጅትና ትግበራ፣ የተቋማት ንብረት አስተዳደር፣ የግዥ አስተዳደር፣ የሰው ሃብት አስተዳደር፣ የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ፣ የፕሮጀክቶች አስተዳደር፣ የኦዲትና ቁጥጥር ሥርዓት ክፍተቶችን በመፈተሽ፣ የሙስና ስጋቶችን በመለየትና የማሻሻያ ምክረሃሳብ በማቅረብ የአሰራር ስርዓት እና የፖሊሲ ማሻሻያ ግብዓቶች ማመንጨት ዓላማ አድርጎ ይህ ጥናት በማዕድን ዘርፍ ስር በሚገኙ ተቋማት ላይ ተጠንቷል፡፡

1.2. የዘርፉ አጠቃላይ መረጃ

የማዕድን ዘርፍ "በ2022 የማዕድን ሀብታችን የብልጽግና መሠረት ሆኖ ማየት" የሚል ርዕይ ያለው ሲሆን በስሩ የሚከተሉት ተቋማትን ያካትታል፡፡ የኢፌዴሪ ማዕድን ሚኒስቴር፣ የኢትየጵያ ጂኦሎጂካል ኢኒስቲቲዩት፣ የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት ሲሆኑ የተመሰረቱበት የጊዜ በ2014 ዓም እንደ አዲስ በዘርፍ የተደራጁ ሲሆን በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት 495 ሰራተኞችን በመያዝ ርዕዩን ለማሳካት በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

ዘርፉን የሚመራው የማዕድን ሚኒስቴር የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ 1263/2014 የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት አሉት፤

- የማዕድን፣ የጂኦተርማል፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና የሕግ ማዕቀፍ ያመነጫል፣ ለአፈጻጸሙ ከሀገራዊ የልማት አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ ዝርዝር መርሀ-ግብር ያዘጋጃል፤ በሚመለከተው አካል ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
- የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋንና የሥነ-ምድር መረጃዎች ማደራጀትን ሥራን ያስተባብራ፣ መረጃዎችን ለኢንቨስትመንትና ለልማት ተደራሽ ያደርጋል፤
- የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማት ሥራዎችን ለማፋጠን የሚውሉ የቤተ-ሙከራና የማዕድን ጥራት ማረጋገጫ ማዕከላትን እንዲሁም የምርምርና የማሰልጠኛ ተቋማትን እንደአስፈላጊነቱ ያደራጃል፤

- በማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማት መስክ የሚፈለገውን የሰው ሀብትለማልማት ከትምህርት ተቋማትና ከሌሎች የሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት ይሠራል፤
- የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ኢንቨስትመንትና ልማት የግል ዘርፉ ተሳትፎና ሚናን ለማሳደግ የሚያስችል የአሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፣ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፤
- የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ምርት ፍለጋን በበላይነት ይመራል፣ ምርቱን ወደ ገበያ ለማሸጋገር የሚያስችል ዘመናዊ አሠራሮችን ይዘረጋል፤
- ተጨማሪ እሴት ያላቸውን የማዕድን፣ ነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ምርቶች ላይ የሚሰማሩ የውጭ እና የሀገር ውስጥ ባለሀብቶችን የኢንቨስትመንት እና ማምረት አቅም ለማጎልበት የምርምር፣ የክህሎት ልማት እና የቴክኖሎጂ ሽግግር ሥራዎችን ያበረታታል፣ ይደግፋል፤
- በማዕድን፣ በጂኦተርማል፣ በነዳጅና በተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ፣ የማዕድን ግብዓቶችን በዋነኛነት ተጠቅሞ የኢንዱስትሪ ውጤቶችን በማምረት ሥራዎች ለሚሠማሩ የሀገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶች እና ኩባንያዎች አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት ፈቃድ ይሰጣል፣ የክፍያ ግዴታቸውን መወጣታቸውን ይከታተላል፣ ተገቢውን ድጋፍ ያደርጋል፤ ያስተዳድራል፤
- ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታቸው ጉልህ የሆኑ እና ከውጪ የሚገቡ ማዕድንና የማዕድን ውጤቶች የሆኑ የሲሚንቶና ድንጋይ ከሰል፣ ሴራሚክ፣ ማርብልና ግራናይት፣ የብረት ማዕድን፣ የተለያዩ ኮንስትራክሽን ግብዓቶች፣ የፖታሽና የማዳበሪያ እና፣ የፔትሮሊየም ልማት ውጤቶች በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣ የምርመራና የምርት ፈቃድም ይሰጣል፣ ከፍለጋ እስከ ምርት ያለውን የምርት ሰንሰለት ውጤታማ እንዲሆን ሙሉ ድጋፍ ያደርጋል፤
- የማዕድን ምርቶች የጥራት ደረጃቸውን የጠበቁ፣ በዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የአቅም ግንባታ፣ የምርምርና ልማት ሥራዎች እንዲከናወኑ ሥርዓት ይዘረጋል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤
- ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር በባህላዊ መንገድ የሚመረቱ ማዕድናት ቴክኖሎጂን በመጠቀም ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችል ውጤታማና ቀልጣፋ የአሠራር ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፤

- ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር በባህላዊና በአነስተኛ ደረጃ የሚመረቱ የከበሩና ጌጣጌጥ ማዕድናት ምርትና ግብይት ሕጋዊ መስመር እንዲይዝ አስፈላጊ ሥርዓትና መሠረተ ልማቶችን ይዘረጋል፤
- የማዕድንና ነዳጅ ሥራዎች በሚከናወንበት አካባቢ የአካባቢ ማህበረሰብን ተጠቃሚነትን የሚያረጋግጡ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፤የሕግ ማዕቀፍ ያመነጫል፣ በሚመለከተው አካል ሲጸድቁም በአግባቡ መፈጸማቸውን ያረጋግጣል፣ በአካባቢ ጥበቃ የተቀመጡ መስፈርቶችን መሟላታቸውን ይከታተላል፤

1.3. የጥናቱ ዓላማ

አጠቃላይ ዓላማ፦

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በማዕድን ዘርፍ ሥር በሚገኙ ተቋማት የአሰራር ስርዓት በመገምገም የሙስና ተጋላጭነት ግምገማዊ ጥናት ማካሄድ ነው፡፡

ዝርዝር አላማዎች፦

- የዘርፉን አሠራሮች ከሙስና ስጋት አንጻር መፈተሽ፣
- የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን፣
- ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን ማቅረብ፣

1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ የሙስና ስጋት ጥናት ከህዳር/06/2015ዓም እስከ ሚያዚያ/30/2015ዓም የኢፌዴሪ ማዕድን ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ማዕድን ኢንዳስቲሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ልማት ኢንስቲቲዩት ተቋማት ላይ ተቋማዊ ተጠያቂነት፣ ግልፅነት፣ አዋጅ ደንብና መመሪያ፣ የተቋማት ንብረት አስተዳደር የግዥ አስተዳደር፣የሰው ሃበት አስተዳደር፣ የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ፣ የፕሮጀክቶች አስተዳደር እና ኦዲትና ቁጥጥር የአሰራር መርሆችን መሰረት በማድረግ የተካሄደ ነው፡፡

1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት

የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በአሰራር እና የስራ ሂደቶች ውስጥ የሚታዩ ድክመቶችና ብልሽቶች በመለየት የሙስና ቅደመ መከላከል እድል ስራዎች ለመተግበር የሚግዝ መሳሪያ ነው፡፡ ዋናው የግምገማዊ ጥናቱ አላማም የሙስና ስጋቶች በተጨባጭ መረጃ በተደገፈ በመለየት የመከላከል ስልቶችን እና ፖሊሲዎችን ለመንደፍ ማስቻል ነው፡፡ እንዲሁም በጊዜ ሂደት የሚፈጠሩ የአደጋ ለውጦችን ለመከታተል ለፀረ-ሙስና ትግል ሥራ እንደ መነሻ ሆኖም ሊያገለግል ይችላል፡፡ በዚህ መሻነት ይህ ጥናት በማዕድን ዘርፍ የሚታዩ የሙሰና ስጋቶች በአስራ አንድ የትኩረት ጉዳዮች ለመየት የተካሔደ ነው፡፡ ይህ የሙስና ስጋት ጥናት ዋና ፋይዳው በማዕድን ዘርፍ የሚሰሩ መንግስታዊ ተቋማ የአሰራር ስርዓቶችን በመፈተሽ፣ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ የስራ ዘርፎችንና የአሰራርር ስርዓቶችን በመለየት፣ የማሻሻያ ምክረ ሃሳብ በማመንጨት የሙስና መከላከል ስልት ማመላከት እና በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አሰራርን መከላከል ያስችላል ተብሎ ይታመናል፡፡

ክፍል ሁለት

ተዘማጅ ፅሁፎች ትንተና

የማዕድን ዘርፍ በተለይ በቴክኒክ ውስብስብነቱ፣ በግሉ እና በመንግስት ሴክተር መካከል ያለው ግንኙነት እና ከፍተኛ ገቢ የሚያስገኝ በመሆኑ ለሙስና ተጋላጭ ያደርገዋል፡፡ በማዕድን ዘርፍ ውስጥ የሙስና አደጋዎች በእያንዳንዱ የእሴት ሰንሰለት ማለትም ኮንትራቶች እና ፈቃዶች መስጠት፤ በሰራዊች ክትትልና ቁጥጥር፤ የግብር እና የሮያሊቲዎች ስብስብ፤ እና የገቢ ክፍፍል እና አስተዳደ ሊያጠቃልል ይችላል (Zuniga, 2019) ፡፡ በዚህ ምክያት ፖለቲከኞችና ባላሃብቶች በሚደርጉት ትስስር ከዘርፉ የሚገኘው ጥቅም ለመጋራት የማመቻመቻ ክፈያዎች ሊፈፀም ይችላል፡፡ ምንም እንኳን ለውጭ የመንግስት ባለስልጣናት እነዚህ የማመቻቸት ክፍያዎች በብዙ የምዕራባውያን ማዕድን ኩባንያዎች የቤት ውስጥ ህጎች የተፈቀዱ ቢሆኑም በአጠቃላይ በሚመለከተው ሀገር ውስጥ ሕገ-ወጥ ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው፡፡ በርግጥ በእነዚያ የውጭ አገሮች ያለው ህግን ተግባረዊ የማድረግ ውስንነት በብዙዎቹ የማመቻቸት ክፍያዎች የተለመዱ ናቸው (Marshall, 2001)፡፡ ሌላው በማዕድን ዘርፍ የሚስተዋለው ሙሰና ውልና ፍቃድ ለአልሚዎች በመሰጠት ሂደት ውስጥ የሚከሰት ነው፡፡ የሚሰጡት ፍቃዶች ግልፅነት በጎደለው መልኩ ስለሚሆኑ በተለይ በማደግ ላይ ባሉ አገሮች አከባቢ ተፅኖ ግምት ውስጥ ያላስገቡ ስለሚሆኑ

ህብረተሰቡን ለጉዳት የመዳረግ ዕድላቸው የሰፋ ያድረገዋል፡፡ ፍቃድ ሰጪው አካልም አጋጣሚውን በመጠቀም የግል ፍላጎቱን ሊያስቀድም ይችላል (Carcamo,2018)፡፡

በዘርፉ ከሚታዩ የሙሰና መገለጫዎች አንዱ በአንድ አገር ውስጥ የሚገኙ የፖለቲካ ንክኪ ያለቸው ሰዎች የሚፈጥሩት ተግዳሮት ከፍተኛ ነው፡፡ የፖለቲካ ንክኪ ያላቸው ሰዎች እንደ ርዕሰ መስተዳድር ወይም መንግሥት፣ ከፍተኛ ፖለቲከኞች፣ የፍትህ ወይም የጦር ኃላፊዎች፣ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ወይም አስፈላጊ የፖለቲካ ፓርቲ ኃላፊዎ እና ቤተሰቦቻቸው የሚያጠቃልል ነው፡፡ በያዙት ስልጣን ወይም ንክኪ ምክንያት ደንቦችን፣ መመሪያዎችን እና ፖሊሲዎችን አላግባብ ጥቅም ላይ በማዋል ወይም ችላ ማለት ደካማው የቁጥጥር ስርኣት መዘርጋት የተፈጥሮ ሀብት በቅናሽ ለባለ ሃብቶች በማቅረብ የሙስና አደጋን ያጎላሉ፡፡ በሌሎች ዘርፍ እነዳሉ ሁሉ በማዕድን ዘርፍም የላቸው ሚና ከፈተኛ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች የበር አሳላፊ ሚና ስለሚኖራቸው የሚሰጡ ፍቃዶች የማሳለጥና የማሰናከል ስራ በመስራት ዘርፉን ለሙስና ተጋላጭ ሊያድረጉት ይችላሉ፡፡ ይህም ለንግድ ድርጅቶች ተገቢ ያልሆነ ትርፍ እንዲያካብቱ የማመቻቸት ስራም ይሰራሉ (Greenpeace (2014))፡፡

ክፍል ሶስት

የጥናቱ መረጃ አሰባስብ ሂደትና ትንተና ዘዴ

3.1. የጥናቱ ንድፈ-ሃሳብ (Research design)

ሙስናና ብልሹ አሠራር በማዕድን ዘርፍ የሚያደርሰውን የሙስና ሥጋት ጥናት ለማካሄድ በአብዛኛው ዓይነታዊ እና በተወሰነ ደረጃ የአሃዛዊ (mixed approach) የጥናት ዘዴዎችን በማጣመር በመጠቀም ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ ለጥናቱ ግብዓት የሚሆነው መረጃም ከየካቲት 8 እስከ ሚያዝያ 14 ቀን 2015 ዓ.ም የመሰብብ ስራ ተሰርቷል፡፡

3.2. የጥናቱ ተሳታፊዎች እና የንሞና ዘዴ (Study Participants and Sampling)

ይህ ጥናት በዋነኝነት በማዕድን ዘርፍ በሚገኙ ሶሥት (3) ተቋማት ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ የተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል፣ የሰው ሀብት አስተዳደር፣ የግዥና ፋይናንስ አስተዳደር፣ የህግ አገልግሎት፣ የለውጥና መልካም አስተዳደር፣ የአይሲቲ የጥናት መረጃ ምንጮች በመሆን አገልግለዋል፡፡ የዚህ ጥናት ዘዴ ከወሳኝ የናሙና አመራረጥ ዘዴዎች መካከል የሆነውን ዓላማ ተኮር ዘዴን በመከተል የጥናቱ ተሳታፊዎችን የለየ ሲሆን በተቋማት ውስጥ ባሉ አሠራሮችና የስራ ሂደቶች ውስጥ ለሙስና ሥጋት የሚሆኑ የአሠራር ክፍተቶችን ግምት ውስጥ በማስገባት የተከሄደ ጥናት ነው፡፡

3.3. መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች (Data collection methods)

3.3.1 የዝግጅት ምዕራፍ

በዚህ በዘርፍ ሥር በተደራጁት ተቋማት ውስጥ ለሙስና ሥጋት ሊሆኑ የሚችሉ 11 የትኩረት ርእሰ ጉዳዮችን የመለየትና በቅደም ተከተል በማስቀመጥ የመረጃ መሰብሰቢ መጠይቅ ተዘጋጅቷል፡፡ በመጠይቅ ዙርያ ላይ ለመረጃ ሰበሳቢዎች ስልጠና በመስጠት ወደ መረጃ መሰብሰብ ስራ ተገብቷል፡፡ የተሰጡት ስልጠናዎችም ተጨባጭ የሠነድ ፍተሻ በማደረግ መረጃዎች ለመሰብሰብ እንዲቻል ለጥናት ቡድን አባላት ግንዛቤ በመፍጠር መረጃ የመሰብሰብ ስራ ተሰርቷል፡፡ ለጥናቱ ግብኣት የሚሆነው መረጃ የተሰበሰበባቸው የትኩረት ርዕሰ ጉዳዮችም ዝርዝር በሚቀጥለው ንኡስ ርእስ ቀርቧል፡፡

3.3.2 የሙስና ሥጋት መንስኤዎችንና አመላካቾችን ልየታ

የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቅ ሲዘጋጅ ታሳቢ የተደረገው በተቋማት ውስጥ የሙስና ስጋት ሊያሳዩ የሚችሉ አመላካች ርዕሰ ጉዳዮች መለየት ነው፡፡ በዚህ እሳቤ መነሻነትም አስራ አንድ ተለየይተው የመረጃ መሰብሰቢያ መጠይቁ ተዘጋጅቷል፡፡ በዘርፉ በተደራጁት ተቋማት የትኩረት ርዕሰ ጉዳዩ ባለመከናወኑ ወይም ሲከናወን የተስተዋሉ ችግሮችን ከሙስና እና ብልሹ አሠራር አንፃር በመቃኘት የሙስና የስጋት መንስኤዎች ወይም አመላካች መረጃዎች መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በመረጃ መሰብሰቢያው መጠይቅ ውስጥ የተካተቱ ትኩረት የተሰጣቸው ርዕሰ ጎዳዮች በዝርዝር እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- **ተቋማዊ አደረጃጀት፡-** ተቋማት ሙስና እና ብልሹ አስራርን ከመከላከል አንፃር ያላቸውን ተቋማ ዊ አደረጃጀትና የአሰራር ስርዓት የሚፈትሽ የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ተጠያቂነት፡-** ተቋማት ተልዕኳቸውን የህግ የበላይነትን በማረጋገጥና ተጠያቂነትን ለማስፈን የህግ ጥሰቶችን በህግ ስርዓት በማስተካከል ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንፃር ያላቸውን ስርዓት የሚፈትሽ የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ግልፅነት፡-** የመንግስት ተቋማት የተቋቋሙበት ዋና አላማ ለህዝብ አገልግሎት መስጠት እስከሆነ ድረስ ተግባር፣ሃላፊነታቸውና የአሰራር ስርዓታቸውን ለተገልግጋዩ ማህበረሰብ ግልፅና ተደራሽ ማድረግ አለባቸው፡፡ በዚህም መሰረት የተቋማት አገልሎት አሰጣጥ ስርዓትና የተደራሽነት መርሆች ምን እደሚመስሉ የሚፈተሸበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ፡-** ሙስና እና ብልሹ አሰረሰርን ለመከላከል፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣አፈፃፀምንን ለማሻሻል ተቋማት የአሰራር መመሪያ፣ አዋጅና ደንብ ያወጣሉእንዲሁም በየ ጊዜው ያሻሽላሉ፡፡ በዚህም መሰረት የተቋማት ቁመና ምን እንደምሚስልና የሚያወጧቸው የአሰራር መመሪያዎች ምን ያክል ሙስና እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ስለመሆናቸው የምንፈትሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ንብረት አስተዳደር፡-** የዘርፉ ተቋማት አገልግሎት የሚሰጡም ሆነ አገልግሎት የማይሰጡ፣ መወገድና መጠበቅ ያለባቸው የተቋማት ንብረቶች የተያዙበት ስርዓት ምን እንደሚመስሉ የሚፈተሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡

- **ተቋማዊ የግዥ አስተዳደር፡** ግዥ በእቅድ፣በመመሪያና በቴክኖሎጅ በታገዘ መልኩ በመፈፀም ብልሹ አሰራርን የሚከላከሉበትን ስረዓትና አሰራር የመፈተሸበት የጥኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ሰው ሃብት አስተዳደር፡** አቅምና ብቃት ያለው የሰውሃበት መረጃ አያያዝን እንዲሁም ከሙስና እና ብልሹ አሰራር የፀዳ የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃ የሚያስተዳድሩብትን ስርዓት የሚፈትሽ የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ሀብት ምዝገባ፡ ሀብት** ምዝገባ አንዱ የግልፅነትና ተጠያቂነት ማረጋገጫ መርህ ስለሆነ የተቋማት አመራርና ሰራተኞች ሀብታቸውን ስለማስመዝገባቸው የምንፈሽበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ ፕሮጀክት አስተዳደር፡** ተቋማት የሚያስተዳድሯቸውን ፕሮጀክቶች የሚያስተዳድሩበትና የሚቆጣጠሩበት ስርዓት ብክነትን በቀነሰ እንዲሁም ከሙስና እና ብልሹ አሰራር በጸዳ መልኩ ስለመሆኑ የምንገመገምበት የትኩረት መስክ ነው፡፡
- **ተቋማዊ የኦዲት ቁጥጥር፡** የውስጥና የውጭ የኦዲት ግኝቶችን የሚገመገሙበት፣ ውይይት የሚደረግበት እንዲሁም የማስተካያ አስራሩ ምን እንደሚመስል ተቋማት የሚገመገምበት የትኩረት መስክ ነው
- **የተቋማትን ልዩ ተልዕኮ መሰረት ያደረገ የሙስና ተጋላጭነት ስጋት ልየታ፡** ተቋማት የጋራ ከሚያደርጓቸው የድጋፍ የስራ ክፍሎች በተጨማሪ የተቋቋሙት ልዩ ተልዕኮ ያላቸውን የተጋላጭነት ሁኔታ የተለየ የሚያደርገው በመሆኑ ልዩ የሆኑት የሚታዩበት የትኩረት መስክ ነው፡፡

3.4. የመረጃዎችን ትንተና ዘዴ

የተሰበሰበው መረጃ ከመተንተቱ በፊት ከየተቋማቱ መረጃዎች በርእሰ ጉዳች ከተለዩ በኂላ የማደራጃት ስራ ተሰርቷል፡፡ ከተደራጀው የሰነድ መረጃ ለማውጣት (extract) እንዲቻል በየዘርፉ የጥናት ቡድኖች ተዘጋጅተው ስራው እንዲሰራ ተደርጓል፡፡ መረጃው በማውጣት ሂደትም በተለዩት ርእሰ ጉዳዮች ዙርያ ተቋማቱ ማከናወን ሲገባቸው ያለከናወኑት ተግባር፣ ተግባራቱን ሲያከናወኑ የተስተዋሉ ችግሮችንና ችግሮችን ለመፍታት የተወሰዱ እርምጃዎች እንዲሁም በተግባራት ክንውን ወቅት የተስተዋሉ ለሙሰና የተጋለጡና ብልሹ አሰራሮች ለመለየት አስችሏል፡፡ የተሰበሰቡ መረጃዎች ለመተንተን እንዲቻል ከአሉት ዓይነታዊ መረጃ

አተናተኖች ውስጥ ጭብጥ ተኮር (Thematic Analysis) ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ የጥናቱ ሪፖርት አቀራረብም አይነታዊ ገለፃ ዘዴ (Descriptive Method) ተግባራዊ የተከተለ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በትንተናው ሂደትም መረጃዎች በመሰብሰብ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮች ወይም ተግዳረቶች ግምት ውስጥ ለማስገባት ተሞክሯል፡፡ ይህም ድምዳሜ ላይ ከመድረሳችን በፊት ጥንቃቄ እንድናደርግ ያግዛል ተብሎ ይታመናል፡፡

ክፍል አራት

የሙስና ስጋት ትንተና

የማዕድን ዘርፍ የሙስና ስጋት ተጋላጭነት ጥናት ትንተና ተቋማዊ አደረጃጀት፣ የተጠያቂነት ስርዓት፣ የተቋማት ግልፅነት፣ የአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ዝግጅትና ትግበራ፣ የተቋማት ንብረት አስተዳደር፣ የግዥ አስተዳደር፣ የሰው ሃብት አስተዳደር፣ የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ፣ የፕሮጀክቶች አስተዳደር እና የኦዲት ቁጥጥር የአሰራር ሥርዓት የኢፌዴሪ ማዕድን ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ ማዕድን ኢንዳስቲሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ልማት ኢንስቲቲዩት ተቋማቶችን አፈፃፀም በመዳሰስ አንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ማስታወሻ፡ የማዕድን ዘርፍ ስር የሚገኙ የኢትዮጵያ ማዕድን ኢንዳስቲሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ልማት ኢንስቲቲዩት ተቋማት የስነምባር መካታተያ ክፍልንና ሌሎች ደጋፊ የስራ ክፍሎችን ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር በፖል እንደሚጠቀሙ ግምት ውስጥ ማስገባት ተገቢ ነው፡፡

4.1. ተቋማዊ አደረጃጀት

የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 1236/2013 ክፍል 3፣ 20(1) መሰረት በየደረጃው በሚገኙ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና በመንግስት የልማት ድርጅቶች ውስጥ የሥነ-ምግባር ተግባራትን እና የሙስና መከላከል ስራን የሚያስተባብር እና የሚፈፅም የሥነ-ምግባር መከታተያ የስራ ክፍል እንደሚደራጅ ተመላክቷል፡፡ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ ለሶስቱም ተቋማት (የኢፌዲሪ ማዕድን ሚኒስቴር፣የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት እና የማዕድን ኢንዱስትሪ ልማት

ኢንስቲትዩት) አዋጁ በሚፈቅደዉ መሰረት ሳይሆን በፑል ደረጃ የተቋቋመ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በመሆኑም በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በማዕከል ደረጃ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የተደራጀ ሲሆን፣በሁለቱ ተጠሪ ተቋማት አልተደራጀም፡፡ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ ቁርጥ በጀት (የራሱ የበጀት አርዕስት) የሌለዉ ሲሆን፣ ለሚያከናዉናቸዉ የተለያዩ ስራዎች የሚያስፈልገዉን በጀት ለድጋፍ ሰጪ ክፍሎች ከተያዘዉ በጀት ይጠቀማል፡፡ ለመከታተያ ክፍሉ ከተፈቀዱት አስር የስራ መደቦች በሰው ኃይል የተደራጁት አራቱ ሲሆኑ፣ አርባ ፐርሰንት ተሟልቷል፡፡ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል ራሱን የቻለ ቢሮዎች ያሉት፣ ለስራ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች የተሟሉለትና ለክፍሉ ተገልጋዮችም አመቺ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ምቹ የስራ ቦታ ከመፍጠር አንፃር በበጎ ጎን የሚታይ ነው፡፡ ክፍሉ የ2015 በጀት ዓመት ዕቅድ አለዉ፣በሁለተኛዉ ሩብ ዓመትም የዕቅድ ክለሳ ተከናዉኗል፡፡ ይሁን እንጂ ዘርፉ ለአገር ካለዉ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ፣ ከሚያንቀሳቅሰዉ ሀብትና ተጋላጭነት አኳያ በዘርፉ ለሚገኙ ሶስቱም ተቋማት የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ የፑል አገልግሎት መስጠቱ ከስራዉ ዉጤታማነት አኳያ አሁን ያለዉ አደረጃጀት ታይቶ መፍትሄ ሊሰጠዉ ይገባል፡፡ ክፍሉ ስራዉን በተገቢዉ መንገድ እንዲያከናዉንም አስፈላጊዉን በጀት መመደብ ትኩረት የሚያስፈልገዉ ጉዳይ ነዉ፡፡

የሃብት ብክነትንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል የሚያስችሉ የተለያዩ አደረጃጀቶች ያሉ ሲሆን ከእነዚህም አደረጃጀቶች መካከል የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፤ የዲሲፕሊን ኮሚቴ፣የቴክኒካል የጨረታ አጣሪ ኮሚቴ፣ የጨረታ ኮሚቴ፣የሰራተኞች ድልድል ኮሚቴ እንዲሁም የስርዓተ ጾታ፣የህግ፣ ተቋማዊ ለዉጥና የዉስጥ ኦዲት የስራ ክፍሎች በአግባቡ ተደራጅተዋል፡፡ በመሆኑም እነዚህ አደረጃቶች መኖራቸዉ በዘርፉ የሃብት ብክነትንና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ያስችላል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ አደረጃጀቶች እና የስራ ክፍሎች የፑል አገልግሎት መስጠታቸዉ ከስራዉ ዉጤታማነት አኳያ አደረጃጀቱ ታይቶ መፍትሄ ሊሰጠዉ ይገባል፡፡

ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ጥቆማዎችን ለመቀበል የሚያስችል ሚስጥራዊነቱን የጠበቀ የአሠራር ሥርዓት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ሙስናና ብልሹ አሠራሮች ሲከሰቱ ጥቆማዎችን ለመቀበል እንዲቻል ስርዓት መዘርጋቱን የጥቆማ መስጫ ኢ-ሜይል፣ ስልክ /6038/፣ ለደንበኞች በአካል ጥቆማ እንዲሰጡ ምቹ የሆነ ቢሮ፣የጥቆማ መስጫ ቅጽ እንዲሁም በተቋሙ ድህረ-ገጽ አማካኝነት የተለያዩ አስተያየቶች ይስተናገዳሉ፡፡ ከተቋሙ ህንፃ ጋር የሚመጥን

የሀሳብ መስጫ ሳጥን ለማዘጋጀት በሂደት ላይ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም የሀሳብ መስጫ ሳጥን ማዘጋጀት ትኩረት መሰጠት አለበት፡፡

የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ ከህግ ክፍል፣ተቋማዊ ለውጥ እና ውስጥ ኦዲት እና ሌሎች የስራ ክፍሎች ጋር በቅንጅት የሚሰራ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ክፍሎች ከስራቸዉ ባህሪ አንጻር ስራዎችን በቅንጅት ስራዎችን መስራታቸዉ በዘርፉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመዋጋት ከፍተኛ ሚና አለዉ፡፡ የሕግ ክፍል ውሎች ላይ ተከታታይነት ያለው ድጋፍ እንደሚያደርግ እንዲሁም ዉሎች ወደ ተግባር ከመግባታቸዉ በፊት ተገቢው አስተያየት የሚሰጥ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ በተቋማቱ የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነት መኖሩን የሚያሳይ አመላካች ማስረጃ አልቀረበም፡፡

በዘርፍ ካለው አደረጃጀት ሊመነጩ የሚችሉ የሙስና ስጋቶች፦

- የስነ ምግባር ክፈሎች በአግባቡ የተደራጁ አለመሆናቸውን ከተገኘው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ አመራሩ ሙስናን ለመዋጋት ያለው ተሳሽነት በሚፈለገው ደረጃ አለመሆን አመላካች ነው፡፡ በአግባቡ ያለተደራጀ ሰነምግባር ክፍል ስራ በተገቢው መንገድ ይወጣል ተብሎ ስለማይታሰብ በዘርፉ የሚታዩትን ብልሹ አሰራሮችን አጥንቶና ለይቶ እርምጃ ለመውሰድ አዳጋች ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪም አመራሩ በአዋጅ የተጣለበትን ሃለፊነት በመወጣት በኩል የያለው ክፍተት አመላካች ነው፡፡ በተጨማሪም የሰው ሃይል አለሞሚለት ስራን ተከፋፍሎ ለመሰራት የሚስችለው ዕድል ያመከነዋል፡፡
- የስነ ምግባር ክፈሉ የራሱ የሆነ በጀት ርእስ ተመድቦለት ወደ ስራ እየገባ አለመሆኑን ከተሰበሰበው መረጃ ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ይህ ስነ ምግባር ክፈሉ ሚሰረቸው ስራዎች በአመራሩ ፍቃድ ላይ የተመሰረተ ሊደርገው እንደሚችል የሚጠበቅ ነው፡፡ አመራሩ ስነምግባር ክፈሉ የሚጠይቅን በጀት በመፍቀድም ሆነ በመከልከል ክፈሉን ለፍለላጎቱ ማስፈፀሚና ሊውለው ይችላል፡፡ በስነምግባር ክሉ የሚሰሩ ስራዎች አመራሩን ተጠያቂነት ሊያስከትልበት የሚያስችል ስራ ሲሆን በጀት ለመፍቀድ ያለው ፍላጎት ዝቅተና እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ ውጤቱም በስነምግባር ክፈሉ ስራ ላይ በላሙያዎች ሳይሆን አመራሩ የመወሰን እድል ስለሚሰፋው ስራ ለአመራር ጣልቃ ገብነት ተጋላጭ

እንዲሆን ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪም የስነምግባር ክፍሉ ተጠሪነቱ ለተቋሙ አመራር ስለሚሆን ነፃነቱን ጠብቆ የመስራት ዕድሉ አነስተኛ እንዲሆን በር ይከፍታል፡፡ መኮኑኖቹ የማጋለጥ ስራ ቢሰሩ በአመራሩ ተገቢ ያልሆነ እርምጃ ሊወስድብን ይችላል ብሎ ከማሰብ ከሚመንጭ ፍራቻ የሚጠበቅባቸው ሃላፊነት በቁርጠኝነት ለመወጣት አዳጋች ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ የስነምግባር ክፍሉ የራሱ የሆነ በጀት ካለተመደበለት ስራዎችን መስራት እንደማይችል መረዳት ተገቢ ነው፡፡

- አንድ ስነምግባር ክፍል ሁሉንም በዘርፉ ያሉ ተቋማት እንዲካታተል ተደርጎ መደራጀቱም በክትትልና ግምገማ ስራ ላይ እክል መፍጠሩ አይቀርም፡፡ ካለው የሰው ሃይል አለመሟለት ጋር ተያይዞ በክፍሉ ውጤታማ የሆነን ስራ ለመስራት አስቻይ ሁኔታዎች እንዳይኖሩ ያደርገዋል፡፡ ይህ የስነ ምግባር ክፍሉ በአዋጅ የተጣለበትን ሃለፊነት ለመወጣት የሚያስችለውን አቅም ውስን እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል፡፡
- በጥናቱ ሂደት ከታዩት የአደረጃጀት ውስንነቶች አንዱ ጠንካር የህግ ክፍል አለመኖር ነው፡፡ የህግ ክፍሉ አለመጠናከር በተቋማቱ ባለስልጣኖች፣ ሀላፊዎች ወይም የአስተዳደር ክፍሎች የሚደረጉ ውሎች፣የንግድ ስምምነቶች፣ የስራ ጨረታዎች፣ የዕቃ ማቅረብ ውሎች፣ ወይም ሌላ ጥቅሞች ከህግ አንፃር መታየት ካለቻሉ ስልጣንን አለአገባብ መገልገል ሊያስከትል ይችላል፡፡

4.2. ተጠያቂነትን ማስፈን

በማዕድን ሚኒስቴር የስነምግባር መከታተያ ክፍል ለሙስና ተጋላጭ በሆኑ የስራ ክፍሎች የሙስና ስጋት ጥናት ማድረጉን በሰነድ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከተከናወኑ ተግባራት መካከል የሙስና እና ብልሹ አሰራር ምንጮች እና የማድረቂያ ስልቶች ተለይተዋል፡፡ በንብረትና ጠቅላላ አገልግሎት ዳይሬክቶሬትና በግዥና ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት (በሶስት የሥራ ክፍሎች) የዳሰሳ ጥናት ተከናዉኗል፡፡ በሶስት የክልል የማዕድን ቢሮዎች እና በክልሉ ያሉ ኩባንያዎች በተመለከተ ጥናት ተከናዉኗል፡፡ ይሁን እንጂ ጥናቱን ተመርኩዞ የማሻሻል እና የማረም ስራ ስለመሰራቱ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ በመሆኑም ለሙስና ተጋላጭ በሆኑ የስራ ክፍሎች የሙስና ስጋት ጥናቶችን ማካሄድና ተግባራዊ ማድረግ ትኩረት ሊሰጠዉ ይገባል፡፡ የደንበኞች እርካታ በገለልተኛ አካል ስለመጠናቱ ምንም መረጃ አልቀረበም፡፡ በመሆኑም ይህ ስራ አለመከናወኑ የደንበኞች እርካታን ሚዛናዊ በሆነ መልኩ ለመረዳት ያስቸግራል፡፡ ተጠያቂነት ለማስፈን

ከሚያስችሉ ተግባራት መካከል የሥነምግባር ደንብ (Code of conduct) ማዘጋጀትና መተግበር አንዱ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በማዕድን ሚኒስቴር የሠራተኞችና ኃላፊዎች የሥነምግባር መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡ ይሁን እንጂ በሌሎች ሁለት ተቋማት በተናጠል ስለመዘጋጀቱ መረጃ አልቀረበም ፡፡ በመሆኑም የሥነምግባር ደንብ ዝግጅትና ትግበራ ትኩረት ሊሰጠዉ ይገባል፡፡

የተሳሳቱ ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት ጥቆማ ደርሶ የተደረጉ ቅድመ መከላከል ስራዎች እንደተሰሩ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከተከናወኑ ተግባራት መካከል ጥቆማን መሰረት በማድረግ የተለያዩ ንብረቶች በአግባቡ እንዲወገድ ተደርጓል፣በዘርፉ የሁለት ተቋማት የተሽከርካሪዎች የኪሎሜትር የነዳጅ ልኬት ላይ ጥናት ተከናዉኗል፡፡ ግኝቱን መሰረት በማድረግም እርምጃ ተወስዷል፡፡ በስነ ምግባር ጉድለት ምክንያት በአመራሩም ሆነ በፈጻሚ አካላት ላይ የቀረቡ ክሶች እንዳሉ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህ አኳያ በአመራሩ በዲሲፕሊን የቀረቡ ክሶች 3 ሲሆኑ፣ ውሳኔ የተላለፈበት 1 ነዉ፡፡ በተመሳሳይ በፈጻሚዎች በዲሲፕሊን የቀረቡ ክሶች 3 ሲሆኑ፣ ውሳኔ የተላለፈባቸዉ 2 ሲሆኑ 1 በፍርድ ቤት ጉዳዩ እየታየ ነዉ፡፡ በህግ ክፍል ባለፉት ሁለት ዓመታት ክስ ከመመስረትና በተመሰረቱ ክሶች ማሸነፍ አንጻር የተሰራ ስራ የለም፡፡ ባለፉት ሁለት ዓመታት 98 ቅሬታዎች የቀረቡ ሲሆን፣ በቀረቡ ሁሉም ቅሬታዎች ውሳኔ ተላልፎባቸዋል፡፡ ቅሬታዎችም ከሰራተኛ ድልድል፣ከግዥ፣ከክፍያ ጋር የተያያዙ ናቸዉ፡፡ በተጨማሪም ለፀረ-ሙስና ትግል የአመራር ሚና ወሳኝ መሆኑን የተለያዩ የጥናት ውጤቶች ያመለክታሉ፡፡ ከዚህ አንጻር የበላይ ሃላፊዎች የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ክፍልን የስራ ክንውን ግምገማ እንደሚያካሂዱ መገንዘብ ተችሏል፡፡

በማዕድን ዘርፍ ተጠያቂነትን አለማስፈን ተከትሎ ሊፈጠሩ የሚችሉ የሙስና ስጋቶች፡-

- በዘርፉ ባሉ ተቋማት ላይ የተደረገ ጥናት በመረጃ ስብሰባው ሂደት የተጠቀሰ ቢሆንመ በጥናቱ ላይ ተመስርተው ስለ ተወሰዱ እርምጃዎች የተገኘ መረጃ የለም፡፡ ከዚህ በመነሳት መግንዘብ የሚቻለው በዘርፉ አመራር ተጣያቂነት በማስፈን በኩል ቁርጠኝነት ጥያቄ ምልክት ውስጥ የሚካት ነው፡፡ በተለይ የማዕድን ዘርፍ ለሃገሪቱ ካለው አስተዋፅኦ አንፃር ዘርፉ ተጠቂነት ባለው መንገድ ካልተመራ ከማዕድን ማገኘት ያለባትን ጥቅም ከማስቀረቱ በተጨማሪ የሃገር ሃብት አለአግባብ ለግል ጥቅም ሊውልበት የሚስችል ሁኔታ ሊፈጠር

ይችላል፡፡ ስለዚህ የተደረጉት ጥናቶች ጥልቅ በሆነ መልኩ ማካሄድና ለሚፈጠሩ ጥፋቶች ተጠያቂ አካለትን መለየትነሰ ተጠያቂ ማድርግ ከአመራሩ ቁርጠኝነት ይጠይቃል፡፡

- በዘርፉ ተቋመት የደንበኞች እርካታ በገለልተኛ አካል ለማስጠናት ያካሄዱት እንቅስቃሴ አለመኖሩ ተጋልጋዮች የሚያጋጥማቸው ችግሮች ለመፍታት የሚስችለውን እድል ሊያመከነው ይችላል፡፡ ብዙ የሚስና ጉዳዮች የሚከሰቱት በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት የሚከሰቱ በመሆናቸው ከተገልጋዮ የበለጠ በመስና ጉዳይ የመረጃ ምንጭ ሊሆን የሚችል የለምና፡፡ በተለይ ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠትና ማቀባበል ጋር ተያይዞ የሚነሱ ብለሹ አሰራሮች ከተገልጋዮች ስለሆነ የሚገኘው የተቋም አመራር ጥናት ማካሄዱ ትኩረት ሊሠጠው የሚገባው መሆኑን ጉዳይ መገንዘብ ይጠበቅበታል፡፡ አለአግባብ የሚንተቱ ጉዳዮች በተቋመት ሲከሰቱም ዋናው የመረጃ ምንጭ ተገልጋይ መሆኑን ተገልጋይ ተኮር ጥናት መካሄድ የሙስና ስጋቶች መለየት በይደር የማይታለፍ ጉዳይ መሆኑን ያመላክታል፡፡

4.3. ተቋማዊ ግልጽነት

ተቋማት ራሳቸውን ለተገልጋዮችና ባለድርሻ አካላት ተደራሽ ማድረግ ዓላማቸውን ለማሳካትና አፈፃፀማቸውን ለማሳደግ ሚናው የጎላ ነው፡፡ ግልፅነት ሙስናንና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የሚያስችል መርህ ነዉ፡፡ ግልጽነትን ማስፈን የተቋማትን የተአማኒነት እና ቅቡልነት ለማረጋገጥ ያስችላል፡፡ በመሆኑም ተቋማት አሰራራቸውን ግልፅና አሳታፊ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለውን የግልፅነት ስራዎች በዚህ ክፍል ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡ የዘርፉን ግልፅነት ለማስፈን እንዲያግዝ የተለያዩ ስራዎች እየተሰሩ መሆኑን ከተሰበሰቡ መረጃዎችና እና ምልከታ መረዳት ይቻላል፡፡ የዘርፉ ተቋማት እቅዶች በጋራ ውይይት የሚደረግ እና የዘርፉ የእቅድ አፈጻጸም ግምገማ ብልሹ አሰራሮችን ለመለየት ያስቻለ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ዓመታዊ መደበኛ፣ ካፒታል እና የውስጥ ገቢ በጀት አጠቃቀም መረጃ ለሚመለከታቻው አካላት ተደራሽ ተደርጓል፡፡

በዘርፉ ያሉ የስራ ሂደቶች በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚመለከታቸውን አካላት እንደሚያሳትፉ በሰነድና ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ተቋማዊ ዉሳኔዎች በዘርፉ የበላይ አመራሮች በየሳምንቱ ሰኞ በጋራ እንደሚወሰኑ፣ ሌሎች ኦፐሬሽናል ስራዎች የተመለከቱ ዉሳኔዎች በማኔጅመንት (የበላይ አመራሮችና ስራ አስፈጻሚዎች) በየሳምንቱ አርብ ይታያሉ፡፡ በተመሳሳይ

መልኩ በየሳምንቱ በተጠሪ ተቋማት ማኔጀመንት (በተጠሪ ተቋማት ዋና ዳይሬክተሮች፣ስራ አስፈጻሚዎችና ቡድን መሪዎች) ስራዎች ይገመገማሉ፡፡ በየሶስት ወር የበላይ አመራሮች፣ ጽ/ቤት ኃላፊ፣ስራ አስፈፃሚዎችና ቡድን መሪዎች የሚሳተፉበት የፕሮሰስ ካዉንስል ስብሰባ ይካሄዳል፡፡ በዘርፉ ውሳኔዎች እና ቃለ-ጉባኤዎች በተገቢው መንገድ ተደራሽ ስለመሆናቸዉ ከMining Management Whatsup Group የመረጃ ልዉዉጥ እና ቃለ-ጉባኤ መረዳት ተችሏል፡፡

የግዥና ጨረታ ማስታወቂያዎች በይፋ ስለመሰራጨታቸዉ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ከተጻፉ ደብዳቤዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም መረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ እንዲሆን ስራ እየተሰራ መሆኑን ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት ይቻላል፡ የሚሰራ ዌብ ሳይትና ፌስቡክ መኖሩን፤ ለሚዲያ እና ሌሎች አካላት አስፈላጊ መረጃዎች በተለያዩ ጋዜጣዊ መግለጫዎች፣ በስልክ፣በቴሌግራም፣በፌስቡክ፣ዩቱብ እና በተቋሙ ድህረ ገጽ እየተሰጠ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዘርፉ የተጠናከረ የኮሙኒኬሽን ስራዎች ማከናወን እንዲቻል በሰዉ ኃይል ማደራጀት እና በዘርፉ ሁሉም ተቋማት ትኩረት ሊሰጠዉ ይገባል፡፡

በማዕድን ዘርፍ ግልፅነት አለማስፈን ተከትሎ ሊፈጠሩ የሚችሉ የሙስና ስጋቶች፦

- በጥናቱ ሂደት ተቋማት በየጊዜው ግምገማ ቢካሄዱም ለሰራተኞቻቸው የግምገማ ውጤቶች ለሰራተኞች ተደራሽ መሆናቸውን የሚሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡ የግምገማ ውጤቶች ጊዜያቸወን ጠብቀው ለሰራተኛው ማይደርሱ ከሆነ ግልፀነት አሰራር ሊኖር እንደሚችል አመላካች ነው፡፡ ሰራተኛው ተሰብስቦ ስለ ዕቅድ አፃፀም መወያየቱም የሚሳይ መረጃ አለመኖሩ የተቋማት አመራሮች ግልፅነት በማስፈን በኩል ያላቸውን ዝግጁነት ውስንነት እንዳለው ያመላክታል፡፡
- በዘርፉ ግዢና በጀት የሚተዳደርው በማዕከል (pool) መሆኑን ከተገኘው መረጃ መረዳት ቢቻልም በየጊዜው ለሚመለከታቸው አካለት መረጃ ስለ መቅረቡ አመላካች መረጃዎች አልተገኙም፡፡ ይህም ለፈጻሚ አካለት መረጃ በአግባቡ ስለማይደርስ በሂደቱ ሊከሰቱ የሚችሉ ብልሹ አሰራሮች ለመለየት አዳጋች ያደርገዋል፡፡ በተለይ የግዢ መረጃዎች ተደራሽ ማድረግ ካልተቻለ የሚከሰቱ የጥቅም ግጭቶች የሚመለከት መረጃ በጥቆማ መልክ ለማግኘት የሚስችል ሁኔታ እንዳይፈጠር ሊያደርገው ይችላል፡፡

- ሌላው በዚህ ዘርፍ ከተጠያቂነት ጋር ተያይዞ የሚነሳው ጉዳይ ተቋመተወ ለምርመራ ጋዜጠኞች ክፍት መሆናቸው መረጃ ማግኘት አልተቻልም፡፡ በተለይ ዘርፉ ብዙ ጥያቄ የሚነሳበት እንደመሆኑ መጠን በማዕድን ዙርያ የሚታዩ ብልሹ አሰራሮችን አንጥሮ በማውጣት በኩል የምርመራ ጋዜጠኝነት ያለው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው፡፡ አመራሩ ጋዜጠኞች ሲመጡ መተባበር ብቻ ሳይሆን በዘርፉ ዙርያ የምርመር ስራ እንዲሰሩ የማበረታታት ሃላፊነትም አለበት፡፡

4.4. አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ

በዘርፉ ሙስናን ለመዋጋት ከሚያስችሉ ጉዳዮች መካከል አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ሚናቸው ከፍተኛ ነው፡፡ የህግ የበላይነት ከማስፈን ባሻገር ተግባራዊ መደረግ ያለባቸው መርሆች በመደንገግ ፈፃሚዎች ስራቸውን ህግ በተከተለ መሰረት እንዲሰሩ አስገዳጅ ሁኔታቸውን ይፈጥራል፡፡ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተግባራዊ መደረጋቸውን ክትትል ከማድረግ በተጨማሪ በየጊዜው መሻሻል ይኖርባቸዋል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ውስጥ ከአዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ጋር ተያይዘው የተሰሩ ስራዎችን ከዚህ በታች ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

በዘርፉ ጥናቶችን እና የዕለት ተለት ስራዎችን መሰረት በማድረግ፤ ደንቦች እና መመሪያዎች የመለየትና የማሻሻል ስራዎች መከናወናቸዉን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተጓዳኝ መመሪያዎችን በፍትህ ሚኒስቴር የማስመዝገብ ልምዱም እየዳበረ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡ ፀድቀው የሚወጡ መመሪያዎች ለተገልጋዮች/ለተጠቃሚዎች በድህረ ገፅ አማካኝነት ተደራሽ ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ ለአመራሮች እና ሰራተኞች በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች አተገባበር ላይ ስልጠና እየተሰጠ መሆኑን የሚያመላክት መረጃ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በመሆኑም በተለያዩ ስልጠናዎች በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ላይ የአመራሮች እና ሰራተኞችን ግንዛቤ ማጎልበት በትኩረት ሊሰራ ይገባል፡፡ በመንግስት መስሪያ ቤቶች ለዜጎች የሚሰጡትን አገልግሎት ዉጤታማ፣ቀልጣፋ፣ከሙስና እና ብልሹ አሰራሮች በጸዳ መልኩ ማቅረብ እንዲችሉ ወቅታዊ እና የተሟላ የዜጎች ቻርተር ያስፈልጋቸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር የማዕድን ሚኒስቴርና የተጠሪ ተቋማት የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ (የተገልጋዮች ቻርተር) ተዘጋጅቷል፤ በብሮሽርና በድህረ ገጽ ለተገልጋዮችም ተደራሽ ሆኗል፡፡

በማዕድን ዘርፍ አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ጋር በተያያዘ ሊፈጠሩ የሚችሉ ስጋቶች

- ለአመራሮች እና ሰራተኞች በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች አተገባበር ላይ ስልጠና የመስጠት ባህል አለመኖሩ በአፈፃፀም ላይ ክፍተት ከመፍጠሩ ባሻገር ህጎች ሲጣሱ ለማረምም ችግር መፍጠሩ አይቀርም፡፡ አስፈፃሚው አካልና ተገልጋዩ በህግ ዙርያ ያለው ዕውቀት ውስንነት የሚሰተዋልበት ከሆነ አለአግባብ ስልጣን የመገልገል ስጋቶች ሲኖሩ የቅድመ መከላከል ስራ ተግባራዊ ለማድረግ ችግር ሊፈጥር እንደሚችል ይታመናል፡፡
- አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ተጠያቂነት ለማስፈን ወሳኝ ሚና እንደሚጫወቱ እሙን ነው፡፡ በመሆኑም ተግባራዊ መደረጋቸው ሙስናን ከመከላከል አንፃር ያመጡት ለውጥ ወይም ያሳደሩት ተፅዕኖ መመርመር እና ማጥናት ካልተቻለ ተጠያቂነት ለማስፈን ያላቸውን ጠቃሚነት ጥያቄ ምልክት ውስጥ ያስገባቸዋል፡፡ የተፅዕኖ ጥናት ማካሔዱ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎችን በተጨባጭ መረጃ ተመስርቶ ለማሻሻልና አዳዲስ ህጎች ለማውጣት አስቻይ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በጥናት ላይ ያልተመሰረቱ ማሻሻዎች እና አዳዲስ ህጎች ለብዙ ጉድለቶች የተጋለጡ ሊሆኑ ስለሚችሉ ለመተግበር አስቸጋሪ ከመሆናቸው ባሻገር ለብልሹ አሰራርና ሙሰና መከሰት አስተዋፅኦ ሊያድርጉ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የዘርፍ አመራሮች ህጎች ከማሻሻላቸው ወይም አዲስ ህግ ከማውጣታቸው በፊት አስፈላጊው የተፅዕኖ ዳሰሳ ጥናት ማካሄድ ትኩረት ሊሰጡት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ አሰራሩን ከማዘመን ባሻገር ብልሹ አሰራሮችና ሙስና ለመዋጋት ተጨባጭነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

4.5. የተቋማት ንብረት አስተዳደር

የንብረት አስተዳደር ስርአት ወጤታማነት የሚለካው ንብረቱ በአግባቡ ተጠብቆ አገልግሎት ላይ መዋሉን ማረጋገጥ ሲቻል ነው፡፡ የተገዙ ንብረቶች መረከብን፣ በተገቢው መንገድ ማከማቸትና መጠበቅን፣ ለተጠቃሚዎች ማድረስና ንብረቶቹ ለተገቢው አገልግሎት መዋላቸውን ማረጋገጥ ያጠቃልላል፡፡ በተጨማሪም በየጊዜው የንብረት ቆጠራ ማካሄድ እንዲሁም ተገቢ የሆነ የንብረት አወጋገድ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ይህን ታሳቢ በማድረግ በዘርፉ ውስጥ ካለው የንብረት አስተዳደር ስርአት ጋር ተያይዘው የሚነሱ ጉዳዮችን ለመተንተን ተሞክሯል፡፡

የቀረቡት ሰነዶች የንብረት የማስተዳደርና የመቆጣጠር ስራዎች እየተከናወኑ መሆኑን የሚያመላከቱ ናቸው፡፡ እስቶክ ካርድ፣ቢን ካርድ፣ ቋሚ ንብረት ምዝገባ መከናወኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ የንብረት ቆጠራም በተገቢዉ ሁኔታ መከናወኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ይሁን እንጂ በዘርፉ በሚገኝ አንድ ተቋም የንብረት ቆጠራ ስለመከናወኑ የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፡፡ ከንብረት አያያዝ ጋር የሚጠቀሰው ሌላዉ ጉዳይ የካይዘን ንብረት አስተዳደር ስርዓት ሲሆን ስርዓቱ በተቋማቱ ስለመተግበሩ የሚያሳይ መረጃ አልተገኝም፡፡ ንብረት አያያዝን በተመለከተ ዘመናዊ አሰራር አለመኖር በንብረት አያያዝና ቁጥጥር ስርአት ላይ ክፍተት በመፍጠር የሙስና ስጋት ሊሆን ይችላል፡፡ በተጨማሪም ከተገኘው መረጃ መገነዘብ እንደተቻለው በዘርፉ ስር ባሉ ሁለት ተቋማት የሚወገዱ ንብረቶችን የመለየት ስራ እንደተሰራ ነው፡፡ የሚወገዱ ንብረቶችን ተገቢ ጥበቃ እና አያያዝ እንደሚደረግላቸዉ መገንዘብ ተችሏል፡፡ የሚወገዱ ንብረቶች ዝርዝር ቀርቦ በባለሙያዎች የሚገመገም መሆኑን፣ ንብረቶቹም በእርዳታ/ስጦታን እና በግልጽ ጨረታ የማስወገድ ስራ ተሰርቷል፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረቡት የተቋሙ የንብረት አሰተዳደር ስርአትና አፈፃፀም አኳያ ሊጠቀሱ የሚችሉ የሙስና ስጋቶች፤

- በዘርፉ ያሉ ተቋመት አመታዊ የንብረት ቆጠራ ቀጣይነት ባለው የተደራጀ መንገድ እያካሄዱ አለመሆናቸው ከተገኘው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ ቆጠራው ብክነትን ከመከላከል ባሻግር ስርቆትን ለመከላከል አጋዥ ሚና ሊኖረው እንደሚችል እሙን ነው፡፡ የንብረት አስተዳደር አሰራሩ በተገቢው ጥበቃና ቁጥጥር ካልታገዘ የመንግስት ንብረቶችን ለስርቆት፣ ለብልሽት እና ለቃጠሎ የመዳረግ ሁኔታ ሊፈጥር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ጥቅም ላይ ውለው ወደ ንብረት ክፍል የሚመለሱ ንብረቶችን መስራት መቻል እና አለመቻላቸው በባለሙያዎች ሳይረጋገጥ ገቢ ማድረግም ተቋምን ለሃብት ብክነት ማጋለጡ አይቀርም፡፡ ጥገና ተደርጎላቸው ወደ ስራ ሊገቡ የሚችሉ ንበረቶችን አላግባብ እንዲወገዱ ወይም እንዲከማቹ የሚችሉበት አጋጣሚ ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ በተቋማት ንብረት የሚያስተዳድሩበት መንገድ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን በተጠናከረ መልኩ ለመዋጋት እንዲቻል ተደርጎ መተግበር አለበት፡፡ ይህ በእንዲህ እንዳለ የዘርፉ ተቋማት ተከታታይነት ባለው መልኩ የተሟላ ንብረት ቆጠራ ማከናወን ይኖርባቸዋል፡፡

- ካይዘን ዋና ዓላመው የሀብት ብክነትን መከላከል ነው፡፡ ንብረትን በተደራጀና አሳታፊ በሆነ መልኩ ለማስተዳደርና መቆጣጠር አሰቻይ ሁኔታ በመፍጠር ሁሉም የተቋም የስራ ክፍሎች እና ሰራተኞች ሃብትን በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውል ያግዛል፡፡ ካይዘን አለመተግበሩ እቃዎች በክምችት እያሉና ስራ ላይ ሳይውሉ ተጨማሪ ግዥዎችን በማከናወን አላስፈላጊ ክምችትን በመፍጠር የህዝብ ሀብት ለብልሽት እና ብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡ በተጨማሪም በየተቋማቱ የንብረት አስተዳደር ስርኣቱ በአውቶሜሽን የታገዘ አለመሆኑን ለመግንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም የንብረት አስተዳደር ዘመናዊ አሰራር የተከተላ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡ ይህም ስርቆትና ብክነት ለመከላከል የሚያስችለውን እድል ያመክነዋል፡፡

4.6. የግዥ አስተዳደር

ተቋማት ሥራቸውን በሚፈለገው ጊዜና ጥራት ማከናወን እንዲቻል ግልጽና ተጠያቂነት ያለዉ የግዥ አስተዳደር ያስፈልጋል፡፡ በዘርፉ የግዥ እቅድ ላይ ግምገማ እንደሚካሄድ ከቀረበዉ ማስረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዘርፉ በሚገኙ የ2015 በጀት ዓመት የግዥ ፍላጎት ለግዥ አፅዳቂ ኮሚቴ ስለመቅረቡ፣የቀረበዉ የዉሳኔ ሀሳብ ለበላይ ኃላፊ ቀርቦ ዉሳኔ መሰጠቱን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ግዥ የሚከናወነው በወቅቱ በተቋሙ ስቶክ ላይ ያለውን ንብረት ተመርኩዞ መሆኑንም መረዳት ተችሏል፡፡ በ2014 በጀት ዓመት በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የግዥ አፈፃፀም ላይ ግምገማ መካሄዱን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዘርፉ የግዥ አፈፃፀም ማሳያዎች (በ2014 የበጀት ዓመት) በዕቅድ የተገዙት ያለዕቅድ ከተገዙት በንጽጽር የሚበልጥ ሲሆን፤ከግዥ ዓይነቶች በፕሮፎርማ የተገዙት ከፍተኛዉን ድርሻ ይይዛሉ፡፡ ከግዥ በፊት የገበያ ጥናት ስለመከናወኑ በቃል ቢገለጽም በሰነድ የተደገፈ ማስረጃ አልቀረበም፡፡

የግዥ ሥርዓቱን ለማሻሻል የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ (EGP- Electronic Government Procurement) ማከናወን የላቀ ፋይዳ አለዉ፡፡ ይሁን እንጂ በዘርፉ ዲጂታላይዝድ የግዢ ስርአት ተግባራዊ ለማድረግ ከሚያስችሉ አንዳንድ ስራዎች በስተቀር ሙሉ በሙሉ ወደ ተግባር ስለመገባቱ በማስረጃ አልተረጋገጠም፡፡

በዘርፉ የተቋማት ግዥ ስርአትና አፈፃፀም በተመለከተ ሊጠቀሱ ከሚችሉ የሙስና ስጋቶች የሚከተሉት ይገኙበታል፦

- አብዛኛው የተቋማት ግዢዎች የሚፈፀሙት በፕሮፎርማ የሚገዙ ከፍተኛዉን ድርሻ የሚይዙ ናቸው፡፡ ይህ የግዢ አሰራር በቁጥቁጥ መጠን የሚፈፀሙ ግዢዎች ላይ የተተመሰረተ ስለሚሆን በብዛት ከመግዛት የሚገኘውን የዋጋ ቅናሽ ጥቅም ሊያሳጣ ይችላል፡፡ ስለዚህ ግዥዎችን ሆን ብሎ በመከፋፈል በቁጥቁጥ የግዥ ዘዴ መፈፀም የተከለከለ ነው፡፡ የፕሮፎርማ ወይም ቁጥቁጥ ግዢ የጨረታ ሰነድ መሰብሰብ ስራ በአብዛኛው በቀጥታ በግዢ ሰራተኞች የሚካሄደው በመሆኑ ለጥቅም ግጭት ተጋላጭ የመሆኑ ሰፊ ያደርገዋል፡፡ በዘርፉ ያሉ ተቋማትም የገበያ ጥናት የማካሄድ ልምድ እንደሌላቸው በመረጃ ስበሰባው ሂደት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተለይ ግዢው በገበያ ጥናት ላይ የተመሰረተ አለመሆኑን የተጋነነ ዋጋ የመቅረብ እድሉም ያሰፋዋል፡፡ አስፈላጊው ክትትልና ቁጥጥር ማደረግ ካልተቻልም የግዢ ሰራተኛውም ሂደቱን ተገቢ ያልሆነ ብልጽግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ጥቅም ላይ ሊያውለው ስለሚችል አሰራሩ ለእምነት ማጉደል ሙስና ተጋላጭ ያደርገዋል፡፡
- የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ (EGP- Electronic Government Procurement) በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ አለመደረጉ ከተሰበሰበው መረጃ መገንዘብ ተችሏል፡፡ ኤሌክትሮኒክ ግዥ ፈጣንና ቀልጣፋ የመረጃ ልውውጥ በመፍጠር የግዥ ሂደቶችን ቀላል እና ለአቅራቢዎች ወይም ለንግድ ማህበረሰብ እኩል እድሎችን በመስጠት የመንግስት ግዢን ግልፅነት የተላበሰ በማድረግ ብልሹ አሰራሮችን ለመቀነስ አስተዋፅኦው የጎላ ነው፡፡ ይህ የግዢ አሰራር አቅራቢዎች እንዲመዘገቡ በማድረግ በየጊዜው መረጃ እንዲደርሳቸው በማደረግ በቂ ቁጥር ያለቸው ተወዳዳሪዎች በጨረታዎች እንዲሳተፉ ለማድረግ አስቻይ ሁኔታ ለመፍጠር ያስችላል፡፡ በተጨማሪም ሃላፊነታቸውን ያልተወጡ አቅራቢዎች መረጃ በመስጠትም አጋዥ ሚና ይጫወታል፡፡ የሰው ለሰው ንክኪ ስለሚቀንሰውም የጥቅም ግጭት እንዳይፈጠር ከማድረግ በተጨማሪ የግዥ ሂደቱ ግልፅነት የተላበሰ እንዲሆን ስለሚያደርገው ሊከሰት የሚችለውን ሙስና በማስቀረት ድርሻው ከፍተኛ ነው፡፡

4.7. የሰው ሃብት አስተዳደር

የተቋም ስኬት ከሚወስኑ መሰረታዊ ጉዳዮች መካከል የሰው ኃብት ነው፡፡ ይህ ስኬት የሚረጋገጠው የሰው ኃብት በአግባቡ ማስተዳደር ሲቻል ነው፡፡ ለዚህ የሚያግዙ አሰራሮችና መዋቅሮች መዘርጋት ተገቢነቱ የጎላ ነው፡፡ ይህን ከግምት ውስጥ በማስገባት በዘርፉ ውስጥ ያለው የሰው ሃብት አስተዳደር ተጋላጭነት በዚህ ክፍል ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል፡፡በዘርፉ በሰራተኛ አስተዳደር ክፍል የተለያዩ ኮሚቴዎች የተደራጁ መሆኑን ማረጋገጥ ተችላል፡፡ እነዚህ ኮሚቴዎችም የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ፤የዲሲፕሊን ኮሚቴ፣የቴክኒካል የጨረታ አጣሪ ኮሚቴ፣ የጨረታ ኮሚቴ፣የሰራተኞች ድልድል ኮሚቴ ናቸዉ፡፡

የቅጥር ማስታወቂያዎች በጋዜጣ፣በዉስጥ ማስታወቂያ ተደራሽ መሆናቸዉንም መገንዘብ ተችሏል፡፡ በ2013 እና 2014 የበጀት ዓመት በሰራተኛ አስተዳደር አሰራሮች ላይ ከምደባ (ጂኤጂ) ጋር በተያያዘ 94 ቅሬታ የቀረበ ሲሆን፣ የቀረቡት ሁሉም ቅሬታዎች መፍትሄ የተሰጣቸው መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህም በመነሳት በዘርፉ ቅሬታዎችን በማስተናገድ እና መፍትሔ በመስጠት በኩል የተሰራዉ ስራ በጥንካሬ የሚነሳ ነዉ፡፡ የመንግስት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ዝቅ ከሚያደርጉ እና የተቋማት ተአማኒነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ጉዳዮች መካከል ሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃዎች ናቸዉ፡፡ በመሆኑም ተቋማት የሰራተኞቻቸዉን የትምህርት ማስረጃና የስራ ልምድ ትክክለኛነት የማጣራት ስራ በትኩረት እንዲሰሩ ይጠበቃል፡፡ በዘርፉ የትምህርት ማስረጃዎች የማጣራት ስራ የተከናወኑ ሲሆን ከ497 ሰራተኞች መካከል የ3 ሰራተኞች የትምህርት ማስረጃዎች ሀሰተኛ ሆነዉ በመገኘታቸዉ እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በመሆኑም የትምህርት ማስረጃዎች የማጣራት ስራዎች መሰራቱ በጥንካሬ የሚታይና ለወደፊትም ተጠናክሮ መቀጠል የሚገባዉ ተግባር ነዉ፡፡ የበላይ አመራሮች ስምሪት በሹመት ሲሆን፣ ሌሎች ኃላፊዎች የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ባወጣው መመሪያ መሰረት በዉድድር ላይ የተመሰረተ መሆኑን ከወጡ ማስታወቂያዎችና ቃለ ጉባኤ ምልከታ መገንዘብ ተቸሏል፡፡ በቴክኖሎጂ የታገዘ (Automated) የሰው ሃብት መረጃ አያያዝ ሥርዓት (Integrated Civil Service Management Information System - ICSMIS) ተግባራዊ መሆኑን በተደረገ ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የብቃት ማሻሻያ ስልጠናዎች በተመለከተ በቁጥር 2 ስልጠናዎች ለ12 አመራሮች፣እንዲሁም 12 ስልጠናዎች ለ26 ስልጠናዎች የተከናወነ መሆኑን የተሰበሰበው መረጃ ያሳያል። ይሁን እንጂ ለሥነምግባር ማሻሻያ ስልጠናዎች ትኩረት ያልተሰጠ መሆኑን አመላካች ነዉ። በመሆኑም ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል በስነምግባር ዙሪያ የተለያዩ ስልጠናዎች ማከናወን ፋይዳዉ ከፍተኛ በመሆኑ የሥነምግባር ማሻሻያ ስልጠናዎች ትኩረት በመስጠት መሰራት አለበት።

ከሰው ሀብት አስተዳደር ጋር ተያያዥ የሙስና ስጋቶች

- የትምህርትና የስራ ልምድ ማስረጃዎች ማጣራቱ ስራ በውስን መልኩ እየተሰራ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ሆኖም በዘርፉ ካለው ሰራተኛ ብዛት አንፃር ስንመለከተው የተሰራው የማጣራት ስራ አጥጋቢ ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም። ሃሰተኛ ሰነዶች በመጠቀም የሚቀጠሩ ሰራተኞች በአገልግሎት አሰጣጥ ጥራት ላይ ከሚያስከትለው ጉዳት ባሻገር ሰራተኛው የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሰነድ በማስመሰል የማዘጋጀት ሙስና መፈፀሙ አመላካች ነው። በተጨማሪም ዜጎች ማግኘት ያለባቸውን የስራ እድል በመዝጋት ተገቢው ልምድና እውቀት ዋጋ እንዲያጣ ስለሚያደርገው በመንግስታዊ ቅጥር ላይ አሉታዊ ምስል የመፍጠር እድሉ ሰፊ ነው።
- ዘርፉ ለአገር ካለዉ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታና ከሚያንቀሳቅሰዉ ሀብትና ተጋላጭነት አኳያ የሰዉ ሃብት ብቃት እና ስነምግባር ላይ ያተኮሩ ስልጠናዎችን በመስጠት ክፍተት በዘርፉ እንዳለ መረጃዎች ያመላክታሉ። ይህም ከእውቀት ማነስ የሚፈጠሩ ብልሹ ተግባራት እና ድካማ አፈፃፀሞች በር ይከፍታል። በተለይ በስነምግባር ዙርያ ተከታታይነት ያለው ስልጠና ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ መሆኑን የዘርፉ አመራር መገንዘብ ይጠበቅበታል። ለስልጠ የሚያስፈልግም ሀብት መመደብም ያስፈልጋል።

4.8. የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ

የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ሥርዓት ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል ዓይነተኛ መሳሪያ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በዚህም መሰረት በሃገራችን የህዝብ ተመራጮች፣ተሿሚዎችና የመንግስት ሠራተኞች ሃብታቸውና ንብረታቸውን ማሳወቅና ማስመዝገብ እንዳለባቸው የህግ ግዴታ ተጥሎባቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት በዘርፉ ማስመዝገብ ከሚገባቸዉ 5 አመራር 4 (80%) እንዲሁም ማስመዝገብ ከሚገባቸዉ 490 ሰራተኛ 375 (76.5%) ያስመዘገቡ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው በዘርፉ የሀብት ምዝገባ ሙሉ በሙሉ ማከናወን ትኩረት የሚያሻዉ ጉዳይ መሆኑን ነዉ፡፡ የምዝገባ ሂደቱ በተጠናከረ መልኩ ማካሄድ የሁሉም ሰራተኞች ሃላፊነት ቢሆንም የተቋማት አመራርም የምዝገባ ሂደቱ ቀልጣፋ እንዲሆን ስራ መስራት ይጠበቅበታል፡፡ ውጤታማ ምዝገባ ማካሄድ ምንጩ ያለታወቀ ንብረትና ገንዘብ ለመቆጣጠር የሚያስችል መሆኑን በመገንዘብ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

4.9. የፕሮጀክቶች አስተዳደር

ባለፉት አምስት ዓመታት ፕሮጀክቶች እንደሌሉ የተገለፀ ስለሆነ የመራጃ ትንተና አልተሰራም፡፡

4.10. ኦዲትና ቁጥጥር

ተቋማት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት በተገቢዉ መንገድ እንዲወጡ የተጠናከረ የኦዲት ስራዎች ማከናወን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህ ክፍል የኦዲት አስተዳደር እንደሚከተለው ተተንትኗል፡፡ በ2014 በጀት ዓመት የውጭ/የውስጥ የኦዲት ሪፖርት ግኝት በዘርፉ የሁለት ተቋማት መረጃ የተመላከተ ሲሆን ያልተወራረዱ ሂሳቦች የውጭ በቁጥር 110፣ በገንዘብ 22,421,127.46፤ እንዲሁም የውስጥ በቁጥር 55 በገንዘብ 7,774,425.89 መሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ይህ ያልተወራረደ ሂሳቦች ትኩረት ተሰጥቶት እልባት ሊሰጠዉ ይገባል ፡፡ የውስጥና የውጭ ኦዲት ግኝቶች ላይ ውይይትና ግምገማ እንደተካሄደ በሰነድ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ የኦዲት ሪፖርቶች ተመስርተው ማሻሻያዎች ተደርገዋል፡፡ የኦዲት ሪፖርት ተደራሽነትን በተመለከተ ለሥነምግባር መከታተያ ክፍል እንዲሁም ለገንዘብ ሚኒስቴር እና ሌሎች የስራ ክፍሎች ተደራሽ መሆኑን መገንዘብ የተቻለ ሲሆን፣ በአንጻሩ ለህግ ፣ለተቋማዊ ለዉጥና የመገናኛ ብዙሃን ተደራሽ ስለመሆኑ መረጃዉ አያመላክትም፡፡

ከኦዲትና ቁጥጥር ጋር ተያያዥ የሙስና ስጋቶች

- የኦዲትና ቁጥጥር ስርዓት የመንግስትን ሀብት ከብክነት ለመታደግ፤ የሙስና እና ብልሹ አሰራር ለመከላከል ያለው ሚና ከፍተኛ ነዉ፡፡ በዋናነት አመራሩ በኦዲት ግኝት ተመስርቶ የእርምት እርምጃ መውሰድ ይጠበቅበታል፡፡ ሆኖም ግኝት ላይ ተመስርተው የተወሰዱ እርምጃዎች የሚሳይ መረጃ በዘርፉ ስር ካሉ ተቋማት ማግኘት አልተቻለም፡፡ የውስጥ ሆነ የውጭ ኦዲት ሪፖርቶች ለሰራተኞች በቀላሉ ተደራሽ መሆናቸው የሚያሳይ መረጃም አልቀረበም፡፡ ሪፖርቶች ተደራሽ አለመሆናቸው አመራሩ አሳታፊ በሆነ መልኩ ብልሹ አሰራሮችን ለመዋጋት ያለው ተነሳሽነት ውስን መሆኑን አመላካች ነው፡፡
- የኦዲት ሪፖርት በተመለከተም ጉዳዩ ለሚመለከታቸዉ አካላት በተለይም ለሥነምግባር መከታተያ ክፍል፣ ለህግ ፣ለተቋማዊ ለዉጥና የመገናኛ ብዙሃን በተደራጀ መልኩ ተደራሽ ማድረግ ትኩረት ሊሰጠዉ ይገባል፡፡ ይህም የሙስና ስጋቶች በጋራ በመየት የተቀናጀ ስልትና ፖሊሲ በመንደፍ በተቋም ደረጃ ሙስናን የመከላከል ስራ ለመከወን አስቻይ ሁኔታ ይፈጥራል፡፡ በመሆኑም ሙስና እና ብልሹ አሰራር ከመከላከል አንጻር ከላይ የተጠቀሱት ክፍሎች በቅንጅት እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር ከዘርፉ ተቋማት አመራሮች ይጠበቃል፡፡

4.11. የሙስና ስጋት ልየታ

በዘርፉ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ስጋት የሆኑ የስራ ሂደቶችን፣የመከሰት እድል እና ተጸዕኖን፣የስጋቱ መንስኤዎች የመፍትሄ ሃሳቦች እንደሚከተለዉ ተመላክቷል፡፡

ተ.ቁ	የሙስና ስጋት የሆኑ ሂደቶች	የመከሰት ዕድል	ቢከሰት የሚያመጣው ተጽዕኖ	የስጋቱ መንስኤዎች	የመፍትሄ ሃሳቦች
1.	የግዥና ፋይናንስ	መካከለኛ	ከፍተኛ	• የገቢ ማነስና የአመለካከከት ችግር፣ • ቦታዉ ላይ በተመደቡ ባለሙያዎች የበላይ ኃላፊ ተፅዕኖ ማድረግ፣ • የመንግስት የግዥ ስርዓቱ ለዚህ የተጋለጠ ነዉ፣ • ታማኝና ብቁ የሆኑ ባለሙያዎች በቦታዉ አለመመደብ	• የግዥ ሰራተኛዉን የገቢ መጠን ማሻሻልና የተለያዩ ስልጠናዎችን መስጠት፣ • የበላይ ኃላፊዎች የግዥ ስርዓቱ ዉስጥ ጣልቃ ሳይገቡ ህግና ስርዓቱን ጠብቆ እንዲሄድ ማድረግ፣ • የግዥ ስርዓቱን ማዘመን
2.	የፈቃድ አሠጣጥና አስተዳደር	መካከለኛ	ከፍተኛ	• የገቢ ችግርና የአመለካከት ችግር፣ • የአሰራር ስርዓቱ አለመዘመን፣ • ያልተገባ ጥቅም ፍለጋ	• ባለሙዎችን በአመለካከትና በኢኮኖሚ ማብቃትና መደገፍ • የአሰራር ስርዓቱን ማዘመንና ግልጽ ማድረግ፣ • ጠበቅ ያለ የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን፣

ተ.ቁ	የሙስና ስጋት የሆኑ ሂደቶች	የመከሰት ዕድል	ቢከሰት የሚያመጣው ተጽዕኖ	የስጋቱ መንስኤዎች	የመፍትሄ ሃሳቦች
3.	የማዕድን ልማት	መካከለኛ	ከፍተኛ	• የገቢ ችግርና የአመለካከት ችግር፣ • ያልተገባ ጥቅም ፍለጋና ኃላፊነትን በአግባቡ አለመወጣት	• በቦታዉ ላይ ያሉ አመራሮችና ባለሙያዎች በኢኮኖሚና በአመለካከት የማብቃት ስራ መስራት፣ • ኃላፊነቱን በአግባቡ እንዲወጣ የቁጥጥርና የአሰራር ስርዓት መዘርጋት
4.	የሰዉ ሀብት ብቃት (HR)	መካከለኛ	ከፍተኛ	• አላስፈላጊ ጥቅም መፈለግና ቡድንተኝነት (ዘረኝነት) • የግንዛቤ እጥረትና የአሰራር ስርዓት አለመዘመን	• ከአድልኦ የፀዳ አመለካከት ያለዉ ባለሙያ ማፍራትና በቦታዉ መመደብ፣ • ተከታታይ የሆኑ የአመለካከት ግንባታና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን መስጠት፣ • አሰራሩን ማዘመን

ክፍል አምስት

መደምደምያ እና የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ

5.1. መደምደሚያ

የዚህ ጥናት ዓብይ ዓላማ የነበረው፣ በማዕድን ዘርፍ ሥር በሚገኙ ተቋማት የአሰራር ስርዓት በመዳሰስ የሙስና ተጋላጭነት ግምገማዊ ጥናት ማካሄድ ነው፡፡ በዚህ አቢይ ዓላማ ስር በጥናቱ መቋጫ ላይ ምላሽ ያገኛሉ ተብለው የታሰቡ አምስት የጥናቱ ንኡሳን ዓላማዎችም ነበሩ፡፡ እነዚህም፡- 1ኛ. የዘርፉን አሠራሮች ከሙስና ስጋት አንጻር መፈተሽ፣ 2ኛ. የሙስና ስጋት ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ መተንተን፣ እና 3ኛ. ሙስናና ብልሹ አሠራርን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክረ-ሃሳቦችን ማቅረብ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ ከላይ በሪፖረቱ ላይ ከቀረቡትን አበይት የጥናቱ ውጤቶች መሰረት በማድረግየሚከተለው ድምዳሜ ላይ መድረስ ተችሏል፡፡

1. በዘርፉ አንድ የስነምገባር ክፍል ሦስቱን ተቋማት እንዲከታተል መደረጉ ሳያንስ በበቂ የሰው ሃይል ያልተደራጀ መሆኑን መረዳት ግድ ይላል፡፡ ቅንጅታዊ ለመዋጋት የሚያስችል መደበኛ አሰራር አለመኖሩ እና ስነምግባር ክፍሉ ቀጥተና ተጠሪነቱ ለአመራሩ መሆኑን ውጤታማ ስራ እንዳይ ስራ ሙስናን ለመዋጋት ውጤታማ ስራ አለመሰራቱ ያሳያል፡፡
2. በጥናት ላይ የተመሰረተ ተቋማዊ ተጠያቂነት ስራ እየተሰራ አለመሆኑን በሙስና ስጋት ዙርያ እና በተገልጋዮች እርከታ ላይ ጥልቀት ያላቸው አለመካሄዳቸው እንደማሳያ ሊቅርቡ ይችላሉ፡፡
3. የመረጃ ተደራሽነት ሰራዎችም እስከ ሰራተኛው ድረስ ማረጋገጥ የሚያስችሉ ግልፅነትን ማስፈን የሚያስችሉ ስራዎች መመልከት አልተቻለም፡፡ በአብዛኛው የእቅድና አፈፃፀም መረጃዎችና ሪፖረቶች በከፍተኛና መካከለኛ አመራሩ አከባቢ ላይ ተንጠልጥሎ የመቅረት ልምድ እንዳለ ለማስታዋል ተችሏል፡፡
4. በአዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ዙርያ ለአስፈፃሚው አካል ስለጠና የመስጠት ልምዱ አነስተኛ መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም ህጎችን ለማሻሻልና አዳዲስ ለማውጣት የሚያስችሉ ጥናት ማካሄድ ስራ እተደረገ አለመሆኑን መገንዘብ ተችሏል፡፡

5. በተቋማቱ ያለው የንብረት አስተዳደር ለማዘመን የሚያስችሉ የካይዘን ስርኣት እና የአውተሜሽን ተግባራዊ አለመደረጋቸው ተስተውሏል፡፡
6. አብዛኛው የተቋማት ግዝዎች በቁጥቁጥ መንገድ የሚፈፀሙ መሆናቸውን ከተሰበሰበው መረጃ መረዳት ይቻላል፡፡ በተጨማሪም የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ (EGP-Electronic Government Procurement) በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ አለመደረጉ ተስተውሏል፡፡
7. በዘርፉ ባሉ ተቋማት የአስፈፃሚው ስነምግባር ግንዛቤ ለማሳደግ የሚረዱ ስለጠናዎች አየተሰጠ አመሆኑን መረጃዎ ያመላከታሉ፡፡
8. ሃብት የማሳወቅና ማስመዝገብ ስራ አጥጋቢ ሊባል በሚል ደረጃ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን እና ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት መረዳት ተገቢ ነው፡፡
9. የውስጥ ሆነ የውጭ ኦዲት ሪፖርቶች ለሰራተኞች በቀላሉ ተደራሽ አለመሆናቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ይህም አሳታፊ በሆነ መልኩ ብልሹ አሰራሮች እና ሙስናን ለመዋጋት የሚስችል ሁኔታ አለመፈጠሩ ነው፡፡

5.2. የመፍትሄ ምክረ ሃሳብ

በዚህ ውስን ዳሰሳና ትንተና ጥልቅ ምክረ-ሃሳብ ማቅረብ ቢያስቸግርም የሚከተሉትን ጥቅል የመፍትሄ ሃሳቦች ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

- አሁን ያለውን አደረጃጃት በመፈተሸ የሥነምግባር መከታተያ ክፍሉ ነፃነቱን ጠብቆ (ከአመራሩ ጣልቃ ገብነት) ከሌሎች ክፍሎች በቅንጅት ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመዋጋት በሚስችል ደረጃ የማደራጅት ስራ ቢሰራ፡፡ በተጨማሪም የስነምግባር መከታተያ ክፍሉ ያቀዳቸዉን ተግባራት በተገቢዉ መንገድ እንዲያከናዉን ለክፍሉ ቁርጥ በጀት (የራሱ የበጀት አርዕስት) ሊኖረዉ ይገባል፡፡
- ሙስና እና ብልሹ አሰራር ከመከላከል አንጻር የሥነምግባር መከታተያ ክፍል፣ የዉስጥ ኦዲት፣የህግና ተቋማዊ ለዉጥ የስራ ክፍሎች በቅንጅት እንዲሰሩ ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር ይገባል፡፡
- በተጠናከረ መልኩ ጥልቅ የሙስና ስጋት እና የደንበኞች እርካታን ጥናቶችን በማካሄድ ብልሹ ተገባራትና ሙስናን በመለየጥ ተጠያቂነት ማሰፈን የሚያስቸሉ ስራዎች

መስራት፡ ይህም የጥቆማ ስርኣቱን ሚስጢራዊነቱ በጠበቀ መልኩ ማዘመንና መተግበር፡፡

- የተቋም መረጃ ተደራሽነት ለማረጋገጥ የሚያስችል ዘመናዊና የተደራጀ አሰራር በመዘርጋት ለባለድርሻ አካላት በፍጥነትና በጥራት የሚደርስበት ሁኔታ ማመቻቸት፡፡ የዕቅድ እና አፈፃፀም ግምገማዎች የተቋማቱ ሰራተኞች በሚያሳትፍ መልኩ ተግባራዊ ማደረግ፡፡
- በጥናት ላይ ተመስርቶ አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች ከማሻሻልና ማውጣት በተጨማሪ ለአመራሮች እና ሰራተኞች ስልጠና መስጠት፡፡ ተግባራዊ የሚደረጉ ህጎች የሚያመጡት ተፅኖ ላይ ጥናት ማካሔድ እና አሰፈላጊው ክትትል ማድረግ፡፡
- የንብረት አስተዳደር ስርኣቱ ዘመናዊት እንዲላበስ በአውቶሜሽን የታገዘ የካይዘን ንብረት አስተዳደር ስርዓት ተግባራዊ ማድርግ፤ በተሟላ መልኩ የንብረት ቆጠራ ቀጣይነት ባለው መልኩ ማከናወን፣
- የግዥ ሥርዓቱን ለማሻሻል የመንግስት ኤሌክትሮኒክ ግዥ (EGP- Electronic Government Procurement) ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ ፡፡
- የሰዉ ሃብት ብቃት እና ስነምግባር ግንዛቤ ማሳደግ የሚያስችሉ ስልጠናዎችን ማካሄድና ለስራው የሚያስፈልግም በጀት መመደብም፡፡ የትምህርትና ስራ ልምድ የማጣራቱ ስራም አጠናክሮ መቀጠል፡፡
- በዘርፉ የሚገኙ አመራርና ሰራተኞች ሀብት ምዝገባ በተጠናከ መልኩ ማስቀጠል፡፡
- የውስጥ እና የውጭ ኦዲት ሪፖረቶች ተደራሽ በማደረግ የሙስና እና ብልሹ አሰራር መከላከል ስራ በመስራት የመንግስትን ሀብት ከብክነት መታደግ፤ በሪፖረቶች ላይ ተመስርተው የሚወሰዱ እርመጃዎችም ግልፅነት በተመላበት መንገድ ማሳወቅ፡፡

References

1. Zuniga, Nieves (2019) Corruption Risk Mitigation In The Mining Sector, Transparency International(https://www.jstor.org/stable/pdf/resrep20461.pdf?refreqid=excelsior%3A797005c747070c4a5325686c9b484f1d&ab_segments=&origin=&initiator=&acceptTC=1)
2. Marshall, Ian E. (2001, November) A Survey of Corruption Issues in the Mining and Mineral Sector World Business Council for Sustainable Development (WBCSD).
3. Cárcamo, Paola (2018) Corruption Risks In The Award Of Mining Concessions And Environmental Permits: The Case Of Chile, Mining for Sustainable Development Programme, Chile Transparent International
4. Greenpeace (2014) Coalruption: Shedding Light on Political Corruption in Indonesia's Coal Mining Sector, Jakarta, Indonesia